# የውጭ ኢንቨስትመንት እየጎረፈላት የምትገኝ ሃገር

ዮናስ 06-13-17

እስራኤል ለኢትዮጵያ ገበሬዎች አሁን ካለው አምስት እጥፍ ምርት የሚሰጥ ዘር ድጋፍ ማድረጓን Nocamels.com የተሰኘ ድረገጽ ሰሞኑን አስታውቋል። Fair Planet የተሰኘውና በእስራኤል የሚገኘው የበጎ አድራጎት ድርጅት፣ በኢትዮጵያ የአየር ለውጥን መቋቋም የሚችሉ ዘሮችን ድጋፍ ማድረጉን የሚያመለክተው ይህ ዘገባ፤ በኢትዮጵያ ለምርት የሚውሉት ሀገር በቀል ዘሮች ለበሽታ እና ለተባይ የተጋለጡ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ገበሬዎች ሲቸገሩ እንደነበር ዘግቧል። በእስራኤል ድርጅት የተለገሰው ጥራቱን የጠበቀ አዲሱ ዘር ተባዮችን እና በሽታን የመቋቋም አቅሙ በጣም ከፍተኛ መሆኑን የባለሞያዎችን ትንታኔ ዋቢ ያደረገው ዘገባ አመልክቷል።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች የቻይና ኢንቨስትመንት ድርሻ ከአራት ቢሊዮን ዶላር በላይ መድረሱን የቻይና የዜና አውታር xinhua የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ አቶ መለስ አለምን ዋቢ በማድረግ ያስታወቀ ሲሆን፤ ለ111 ሺህ ኢትዮጵያውያንም የሥራ እድል መፍጠሩን፤ እንዲሁም ኢትዮጵያ የAsian Infrastructure Investment Bank (AIIB) አባል ሀገር ሆና መፈረሟ በተለያዩ ዘርፎች ለምታከናውናቸው የልማት ስራዎች ብድር ለማግኘት እንደሚያስችላት አቶ መለስ መናገራቸውን የዜና አውታሩ በዘገባው አካቷል። የሁለቱ ሀገራት የንግድ ግንኙነት 6.3 ቢሊየን ዶላር መድረሱን እና በየአመቱ የሃያ ሁለት በመቶ እድገት እያሳየ መሆኑም በዘገባው ተመልክቷል።

እነዚህ ከላይ የተመለከቱ ሁለት ዘገባዎች ብዙ ነገር ያመላክታሉ። የኢትዮጵያን አለማቀፋዊ ግንኙነትና ተሰሚነት፤ ይልቁንም የኢንቨስትመንት መዳረሻ እና ሰላማዊት ሃገር መሆኗን። ስለሆነም ነው አንዳንድ ወገኖች የውጭ ኢንቨስትመንት ጎርፍ እያጥለቀለቃት ያለች ሃገር ሲሏት የሚሰማው። በዚህ ፅሁፍ የምናነሳውም ይህ የማያንስባት ስለመሆኑ አመላካች የሆኑ አስረጂዎችን ነው።

በ2016 አፍሪካ ያገኘችው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የቀነሰ ሲሆን የኢትዮጵያ 46 በመቶ ጨምሯል።ይህን የገለጸው ደግሞ የተባበሩት መንግስታት የንግድ እና ልማት

ድርጅት ነው። ድርጅቱ የአውሮፓውያኑን የ2017 ኢንቨስትመንት ትንበያን በተመለከተ ሰሞኑን ይፋ ባደረገው ሪፖርት እንዳመለከተው ያለፈው የፈረንጆቹ ዓመት ማለትም ከጥር ወር 2008 እስከ ታህሳስ ወር 2009 ድረስ ኢትዮጵያ 3 ነጥብ 2 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር መጠን ያለው ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት አግኝታለች። ወደ አፍሪካ የፈሰሰው ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት መጠን በ3 በመቶ ቅናሽ አሳይታል። በአህጉሪቱ ግንባር ቀደም የቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ተቀባይ ሆና የቆየችው እና በነዳጅ ሀብቷ የበለፀገችው አንጎላ 2016 ላይ ያገኘችው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መጠን አሽቆልቁሏል። በአህጉሪቱ ትልቁን ኢኮኖሚ የያዙት ደቡብ አፍሪካ እና ናይጄሪያም በዚሁ ዓመት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ግኝታቸው ቀንሷል። ምስራቅ አፍሪካ ላይ ኢትዮጵያ ያገኘችው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ጠንካራ እድገት የታየበት ሲሆን ይህም ከዚህ ቀደም ያላየችው ነው በማለት የተመድ ሪፖርት ያስረዳል።

በ2016 የምስራቅ አፍሪካ አገራት 7.1 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት አግኝተዋል። ከዚህ ውስጥ ግማሽ የሚሆነውን የወሰደችው ኢትዮጵያ ነች። በአጠቃላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ያገኘችው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መጠን ከቀደመው ዓመት በ46 በመቶ እድገት አሳይቷል። በዚህ መልኩ ኢትዮጵያ የምታገኘው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መጠን እድገት የተቀጣጠለው አገሪቱ በመሰረተ ልማት እና በማምረቻ ኢንዱስትሪው ዘርፍ እያዋለችው ያለው መዋዕለ ንዋይ ነው ይላል የተመድ ሪፖርት።

እንደ ሪፖርቱ በዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ በሚገኙ አገራት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳቢያ የተፈጥሮ ሀብት ነው። ነገር ግን አገራት የኢንቨስትመንት አማራጫቸውን ዓይነት አስፍተው ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ባደረጉት ጥረት እየተሳካላቸው ነው ብሎም ኢትዮጵያን በምሳሌነት አስቀምጧል። ስለሆነም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ጎርፍ እያጥለቀለቃት ያለች ሃገር ብትባል ቢያንስባት እንጂ የሚበዛባት አይሆንም።

ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች በመሰማራት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችሉ በርካታ ዕድሎች አሉ። የሃገሪቱ የተረጋጋ ፖለቲካና ማክሮ ኢኮኖሚ፣ ሰፊ የሰው ኃይልና ርካሽ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቷ በዋናነት የሚጠቀሱት ናቸው። ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የምትከተል በመሆኗ በኢነርጂው ዘርፍ ለመሰማራት

ለሚፈልጉም ሰፊ እድል አለ። ከቀረጥና ኮታ ነጻ እድል መኖሩም ሌላኛው የውጭ ኢንቨስትመንት ጎርፍ ያጥለቀልቀን ዘንድ መነሻ ምክንያት ነው።

የአፍሪካ እና በተለይም ወደብ አልባ አገራት የተፈጥሮ ሀብታቸውን በመጠቀም ከሚስቡት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በተቃረነ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚዋን ተዋፅኦ ዓይነት በማስፋት ከውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ የተሳካላት አገር ለመሆን በቅታለች። በማምረቻ ኢንዱስትሪው መስክ አዳዲስ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እየጎረፈላት የምትገኘው ሃገራችን በሃገራችን የሚገኙ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ከዓለም ገበያ ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ የሚያስችላቸው ይሆናል።

በውሃ ሀብትና በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ በግብርናና በዘርፉ ቴክኖሎጂ ማምረትና ማቅረብ ዘርፎች የተሰማሩ ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸው 13 የእስራኤል ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ያለውን የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚና ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም ኢንቨስት ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውም የዚሁ ማሳያ ነው።

ከላይ ለመነሻ እንዲሆነን በጠቀስነው ዘገባ አግባብ ቻይና ለኢትዮጵያ ቀዳሚዋ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ምንጭ ብትሆንም ከሌሎች አገራትም ባለሀብቶች በኢትዮጵያ በማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ በግብርና ማቀነባበር፣ በሆቴልና ሪዞርት ዘርፎች መጉረፍ ጀምረዋል። ይህንን ጎርፍ ማስተናገድ እንዲቻለን ደግሞ እየተገነቡ ያሉት የኢንዱስትሪ ፓርኮቻችን እየተፋጠኑ እና እየተስፋፉ ነው።

ከ60 ሚሊዮን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ የሚገነባው እና ከሰሞኑ ስምምነት የተፈረመበት የባህርዳሩ ኢንዱስትሪ ፓርክ አንደኛው የማስፋፊያው ማሳያ ነው። ስምምነቱን የተፈራረሙት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንና የቻይናው ሲቪል ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ኮሙኒኬሽን ኩባንያ ናቸው። በስምምነቱ ስምንት የፋብሪካ ሼዶች የሚገነቡ ሲሆን ተያያዥ መሠረተ ልማቶችን ጨምሮ ግንባታው በዘጠኝ ወራት ይጠናቀቃል። የኢንዱስትሪ ፓርኩ 75 ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፍና ደረጃውን የጠበቀ የፍሳሽ ማጣሪያ ቴክኖሎጂን የሚያካትት ነው። በባህርዳር የሚገነባው የኢንዱስትሪ ፓርክም በዋናነት የሰው ጉልበትን በስፋት በመጠቀምና በግብርና ውጤቶች ላይ እሴት በመጨመር ኤክስፖርት ለማድረግ የሚያስችል ሲሆን፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ ከ20 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ይፈጥራል።

በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፎች ያሉትን እድሎች መጠቀም ለሚሹ ባለሃብቶች በተመሳሳይም አገሪቷ በተለያዩ አካባቢዎች የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ገንብታለች፤ ተጨማሪዎችም እየገነባች ነው።

ከአቅም ግንባታ ጋር ተያይዞ በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሥራ የጀመሩት የኢንዶኔዥያዎቹ ታል-ግሩፕና ቡሳና ጨርቃ ጨርቅ ኩባንያዎች በሶስት ዙሮች ከ200 በላይ ኢትዮጵያውያን ሱፐርቫይዘሮች፣ ኦፕሬተሮችና ሰራተኞችን በጃካርታ ማሠልጠናቸው ይታወቃል። በአሁኑ ወቅት ሁለት የኢንዶኔዥያ ባለሐብቶች በኢትዮጵያ የሳሙናና ዲተርጀንት እንዲሁም የህፃናት ምግብ ማምረቻ ፋብሪካዎች ያቋቋሙ ሲሆን በቅርቡ ወደ ማምረት እንደሚገቡ ይጠበቃል፡፡

እነዚህ የኢንዱስትሪ ፓርኮቻችን የሚያስተነፍሱልን እያጥለቀለቀን ያለውን የውጭ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ብቻ ሳይሆን፤ አሜሪካ ለአፍሪካ ሀገራት የሰጠችውን ከቀረጥና ታሪፍ ነፃ የገበያ ዕድል (አጎዋ)ንም ጭምር ነው። አጎዋ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር 2000 ላይ የተጀመረ ሲሆን፤ የአፍሪካ ሀገራት ከ6 ሺህ በላይ የሚሆኑ ምርቶቻቸውን ከታሪፍና ከኮታ ነጻ ወደ አሜሪካ ገበያ እንዲያስገቡ የተመቻቸ እድል ነው። እንደ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃ በሶስቱ አመታት ሃገራችን ከገበያው ከ100 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር በላይ የውጪ ምንዛሬ ብታገኝም የ15 አመቱን ገበያ ከመጠቀም አንፃር አፈፃፀሟ ዝቅተኛ ነው፡፡

ባለፉት 15 አመታት የአፍሪካ ሀገራት በአጎዋ እድል በሚገባ ባለመጠቀማቸው አሜሪካ ፕሮግራሙን ለተጨማሪ 10 አመታት አራዝማዋለች። በእድሉ በአግባቡ ካልተጠቀሙበት የአፍሪካ ሀገራት ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡ የአለም ባንክ ከአሁን ቀደም ባደረገው ጥናት አጎዋ የአፍሪካ ሀገራትን የኢንዱስትሪ ምርቶች በ500 በመቶ ያሳደገ መሆኑን ጠቅሷል። ከተጠቃሚነት አንፃር እንደ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ኢትዮጵያም ገበያውን ባላት አቅም ልክ ካልተጠቀሙ ሀገራት አንዷ መሆኗንም ጥናቱ አመልክቷል፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት በአጎዋ ያልተጠቀመችባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። የሀገር በቀል አምራቾች የአቅም ውስንነት፣ በአሜሪካ ደንበኞች የሚጠየቁ መመዘኛዎችን ያለሟሟላት፣ በውሉ መሰረት በጊዜ ገደብ ያለማቅረብ እና ለግብአት አቅርቦት የውጭ ምንዛሬ እጥረት መኖር ሀገሪቱ ከአጎዋ በሚፈለገው መንገድ ተጠቃሚ እንዳትሆን ካደረጉ ምክንያቶች መካከል ተጠቅሰዋል። በተፈጠረው የንግድ እድል ምርቶችን የማስተዋወቅ ስራና የገበያ ሚዛኑን በመጠበቅ የአሜሪካ ኩባንያ በሃገር ውስጥ እንዲሰሩ የማድረጉ

እንቅስቃሴም ውስንነት ያለበት መሆኑ ሌላኛው ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ እየተገነቡ ያሉት እና ስራ የጀመሩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በቀሪዎቹ ስምንት አመታት ገበያውን ለመጠቀም ተስፋ ተጥሎባቸዋል። የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፓርኮቹን ከአጎዋ እድል ጋር በማቀናጀት ለመንቀሳቀስ ዝግጁነት መኖሩንም በድረ ገጹ ላይ አስፍሯል፡፡

በአለም አቀፍ ደረጃ ገበያቸው በአሜሪካና አውሮፓ የሆኑት እንደ ኤች ኤንድ ኤም እና የፈረንሳዩ ዴካትሎን በሀገሪቱ ቢሮ ከፍተው መንቀሳቀሳቸው የገበያ እድሉን ይበልጥ ለመጠቀም እገዛ የሚኖረው ሲሆን፤ በሚገነቡት አዳዲስ የኢንዱስትሪ ፓርኮችም የአንድ ማእከል የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር የሚኖር መሆኑም ችግሮቹን በማስወገድ በውጭ ኢንቨስትመንት ጎርፍ መጥለቅለቃችንን ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርገዋል ።